የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

HIS IMPERIAL HIGHNESS PRINCE ERMIAS SAHLE-SELASSIE HAILE-SELASSIE
PRESIDENT

# New Year's Greeting from HIH Prince Ermias Sahle-Selassie Haile-Selassie

## President of the Crown Council of Ethiopia

*እንቁጣጣሽ / Enkutatash*
*3 Puagme 2015 / 12 September 2023*

እጅግ ለተወደዳችሁ እና ለተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያንና ትውልዳ ኢትዮጵያ ለሆናችሁ በሙሉ አስቀድሜ እንኳን ከ2015 ወደ 2016 ዓም ቸሩ አምላክ አሸጋገረን ማለት እፈልጋለው።

“እንቁጣጣሽ” ብለን ለብዙ ዘመናት ያከበርነው በዓል መሰረቱ በባሕላችንና በታሪካችን በሐይማኖትም ጥልቅ መሰረት ያለው መሆኑ የታወቀ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንማረው ጥንታዊቷ ንግሥተ ሳባ የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ በመስማቷ ያንን ከእግዚአብሔር ያገኘውን ጥበብ ለማየት እና ለመማር ስትል በረሐ እና ባህር ተሻግራ እየሩሳሌም ድረስ ሄዳ ነበር። ይህ ትግባሯ የተባረከ መሆኑን ለማሳያ በሐዲስ ኪዳንም በማቴዎስ ወንጌል “ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ተነሥታ ከዚች ትውልድ ጋር ትፋረዳለች” ብሎ አምስግኗታል። በዓሉ “እንቁጣጣሽ” የተባለው በዚህ ወቅት ንግሥቲቱ ወደ አገሯ ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ መኳንንቶቿ ብዙ እንቁ አምጥተው እጅ መንሻ ስለ ሰጥዋት ነው ተብሎ ይነገራል። ይህች ታላቅ ንግሥት በዘመን መለወጫ ግዜ ወደ አገሯ ስትመለስ ከንጉሥ ሰሎሞን የሚወለደውን ልጇን ቀዳማዊ ምኒልክን ለመውለድ እየተቃረበች ነበር። በዚህም ምክንያት ዘመን መለወጫ በኢትዮጵያ ለ3000 ዓመት የቆየውና የአገር ኩራት የነበረው የሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት መመስረትም ጋር አብሮ የተሳሰረ ነው። በዚህም ምክንያት አገራቸውን እና ታሪካቸውን የሚወዱ ወገኖቻችን መሙሉ ይሄንን በዓል ሲያከብሩ ነረዋል።

ባለፉት 49 ዓመታት በአገራችን ኢትዮጵያ ታሪኳን የሚያንቋሽሽ፣ አገር በቀል ባሕሏንና የአብሮነትን መሰረት ያደረገውን የኑሮ ፍልስፍናዋን የሚንድ ስራአቶች ተነስተው፣ በባእድ ፍልስፍና፣ በሐሰተኛ ታሪክ፣ አብሮ ተዋልዶ ተጎራብቶ የኖረውን ሕዝብ በማጋጨት ከፋፍለው ለመግዛት በመሞከር ብዙ ችግር ላይ አገሪቷ ወድቃለች። በተለይ በቅርብ ዘመናት በታሪካችን አይተነው የማናውቀው ዘር ተኮር የሆኑ ጦርነቶችና መፈናቀልን አይተናል። እንደዚሁም በቤተ እምነቶች በአብያተ ክርስቲያናት እና በመስኪዶች በሐይማኖት መሪዎች ላይ ታይተው የማያውቁ አስደንጋጭ ክስተቶች ታይተዋል። በዚች 49 ዓምት በአገራችን ላይ የወረደው መአት በታሪኳ አይታው አታውቅም። ለዚህ ችግር መልሱ መከፋፈል ሳይሆን አንድላይነትን ማቀንቀን ነው። ግርማዊ ቀዳማዊ ዐጼ ኃይለ ሥላሴ በ25ኛ ይንግሥ በዓላቸው ላይ አዲስ ሕገ መንግሥት ለፓርላማ ባቀረቡበት ግዜ ሲናገሩ “በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ተወላጅ ዜጎቻችን ሁሉ በመጠናቸው በምክር ቤት ውስጥ በሚገባ እንደራሴ እንዲኖራቸውና በዘርም ሆነ በሐይማኖት በመካከላቸው አንድም ልዩነት እንዳይኖር ለማድረግ ነው። ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ትክክል መብት እንዲኖረውና የተወደደ ሕዝባችን ሁሉ የአንድ ትልቅ ቤተሰብ ተወላጆች ሆነው በወንድማማችነት እኩል እንዲኖሩ ዘወትር የተከተልነው አላማ ነው” ብለው ተናግረው ነበር። አሁንም ቢሆን ከሚለያየን ነገር የሚያተሳስረን የሚያቀራርበን ነገር ስለሚበዛ እንደገና የግርማዊነታቸውን አላማ ዳግም አንስተን የሰላምን የአንድነትን የእኩልነትንና የወንድማማችነትን መንገድ መምረጥ ለአገራችንና ለሕዝባችን ብቸኛው መንገድ መሆኑን ብዙዎች የሚገነዘቡት ይመስለኛል።

አዲሱ ዓመት የሰላም የፍቅር የወንድማማችነት መንፈስ በአገራችን ላይ የሚወርድበትና የሚስፋፋበት እንዲሆን ፈጣሪን ሁላችንም በአንድነት እንድንለምን አሳስባለው። ምህረቱንና ሰላሙን አምላካችን ያውርድልን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ተከብራ ትኑር።

*ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ*
*የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት ፕሬዚዳንት*